## አንቀጽ አንድ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ የሐረር ከተማ ዉኃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለሥልጣን ቦርድ አባላት አበል ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 5/1994 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## አንቀጽ ሁለት

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ

1. «ቦርድ» ማለት የሐረር ከተማ ዉኃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣንን በበላይነት እንዲመራ በማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 26/1993 አንቀጽ 2 መሠረት የተቋቋመ አካል ነው።
2. «አበል» ማለት ለሐረር ከተማ ዉኃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን የቦርድ አባላት ዕውቀታቸውን፣ ችሎታቸውንና ልምዳቸውን በመሰዋት በትርፍ ጊዜያቸው ለድርጅቱ ለሚሠጡት አመራር ማካካሻ ይሆን ዘንድ መጠኑ በክ/ሥ/አ/ኮሚቴ ተወስኖ የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ ማለት ነው።
3. «የቦርድ አባላት» ማለት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 26/1993 አንቀጽ 2 ንኡስ አንቀጽ 4 ከ ሀ እስከ ሰ የተጠቀሱትን የሐረር ከተማ ዉኃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለሥልጣን ቦርድ አባላት ያጠቃልላል።

## አንቀጽ ሶስት

### ለቦርድ አባላት የሚከፈል አበል

የቦርዱ አባላት ከባለስልጣኑ መ/ቤት ገቢ የሚከተሉት አባሎች ይከፈላቸዋል።

1. ቦርዱ በወር ቢያንስ አንድ ጊዜ ወርሃዊ ስብሰባውን ካካሄደ ለቦርዱ ሰብሳቢ ብር 200.00/ሁለት መቶ ብር/ እና ለሌሎች አባላቶች ብር 150.00/መቶ ሃምሳ ብር/ ወርሃዊ አበል ይከፈላቸዋል።
2. እያንዳንዱ የቦርድ አባል ለተገኘበት ለያንዳንዱ ስብሰባ ለሰብሳቢው ብር 50.00/ሃምሳ ብር/ ለአባላቶች 35.00/ሰላሳ አምስት ብር/ ይከፈላቸዋል።
3. በስብሰባው ላይ ያልተገኘ የቦርድ አባል ከላይ የተጠቀሰው አበል አይከፈለዉም ነገር ግን ስብሰባው ላይ ሊገኝ ያልቻለው በቦርዱ የታዘዘውን ሥራ ለማከናወን ሲባል ከሆነ በዚህ አንቀጽ የተመለከተው ክፍያ አይቀርበትም።
4. የቦርዱ የስብሰባ ጊዜ ከመደበኛ የመንግስት የስራ ሰአት ውጭ መሆን ይኖርበታል።

## አንቀጽ አራት

### ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከጥቅምት 1/1994 ዓ/ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ሐረር ጥቅምት 1/1994 ዓ.ም

ፉአድ ኢብራሂም

የሐረሪ ህ/ብ/ክ/መንግስት ፕሬዝዳንት

ሐረር